# መድረክ የአሰራር ችግር ገጥሞታል

(ነጋድራስ ቅፅ 08 ቁጥር 311 ታህሳስ 27 2004 ገፅ 1)

በአሁኑ ጊዜ ስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎቹን ይዞ ወደ ግንባር እየተሸጋገረ የሚገኘው መድረክ የሚቀርቡለትን የአባልነት ጥያቄ ለማስተናገድ አለመቻሉን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለነጋድራስ ገለጡ፡፡

በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትና ተሰሚነት ያላቸውን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አሰባስቦ በዚህች አገር ለሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር ይሰራል ተብሎ የሚታሰበው መድረክ እንደታሰበው እየሄደ አይደለም የሚሉት የነጋድራስ ምንጮች የመድረክ አባልነት ለማግኘት ከሁለት አመት በላይ የሚጠብቁ ድርጅቶች መኖራቸውን ገልጠዋል፡፡

የመድረክ የወቅቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ሞጋ ፍሪሳ ሁለት የደቡብ ህብረት አባል የነበሩ ድርጅቶች ጥያቄ ማቅረባቸውን አስታውሰው መድረክ ውስጥ አባል የሆኑ ሌሎች የደቡብ የፖለቲካ ድርጅቶች በመኖራቸው አዲስ አባልነት የጠየቁ ድርጅቶች ከመድረኩ አባል ድርጅቶች ጋር ያላቸውን ልዩነት ተቀራርበው እንዲፈቱ ማሳሰቢያ መሰጠቱን አስረድተዋል፡፡

# በጅቡቲ ተጨማሪ ወደብ ሊገነባ ነው

*(መሰናዘሪያ ቅ 05 ቁጥር 252 ታህሳስ 17 ቀን 2004)*

ጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የውጭ ምርቶችን የሚያስተናግድ ተጨማሪ አዲስ ወደብ ለማስገንባት የሚውል የ36 ሚሊዮን ዶላር የብድር ስምምነት እንደፈረመች ተገለፀ፡፡

ሮይተርስ የጅቡቲን የበጀት ሚኒስትር አማራህ አሊን በመጥቀስ ባቀረበው ዘገባ እንደሚያመለክተው ወደብ አልባ የሆነችው ኢትዮጵያ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በምታስገባቸውና ወደ ውጭ በምትልካቸው ምርቶች 70 በመቶውን አገልግሎት የምታገኘው በጅቡቲ ወደብ ነው፡፡

ከጅቡቲ ወደቦች በተለይ ለኢትዮጵያ አገልግሎት የሚሰጠውና ኢ.ኤ.አ የካቲት 7/2009 ተከፈተው የዶራሌህ ወደብ የወጪና ገቢ ምርቶችን የማስተናገድ እንቅስቃሴው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ቡታጁራ አዲስ ወደብ መገንባቱ እንዳስፈለገ የሚኒስትሩ መረጃ ይጠቁማል፡፡

ይህን ወደብ ለመገንባት በሚያስፈልገው 61 ሚሊዮን ዶላር ተቀማጭነቱ ኩዌት የሆነ የአገር ልማ ባንከር 36 ሚሊዮን ዶላር ለጅቡቲ ለማበደር መስማማቱንና የሳውድአረቢያ የልማት ባንክ በማቅረብ 25 ሚሊዮን ዶላር ብድር መስጠቱን አስታውቀዋል፡፡

ጅቡቲ ኢዲስ ከምታስገነባው ወደብ በተጨማሪ በዱባይ ካምፓኒ የሚተዳደረው ግዙፉን የጅቡቲ ወደብ ለማስፋፋት 330 ሚሊዮን ዶላር እንደመደበችና ግንባታው በ2014 እንደሚጠናቀቅ ባለፈው ጥቅምት ማስታወቋ ተገልጧል፡፡

# በገጠር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን 100 ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ተሰጠ

*(መሰናዘሪያ ቅ 05 ቁጥር 252 ታህሳስ 17 ቀን 2004)*

የተባበሩት መንግስታት አካል የሆነው አለማቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን በገጠር የድህነት ቅነሳ. ፕሮግራም ለመደገፍ የ100 ሚሊዮን ዶላር እርዳታና ብድር መስጠቱን የተባበሩት መንግስታት የዜና ወኪል በዘገባው አስታውሷል፡፡

እንደዘገባው ከሆነ 50 ሚሊዮን ዶላሩ በብድር መልክ የሚሰጥ ሲሆን ቀሪው 50 ሚሊዮን ዶላር በእርዳታ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ገንዘቡ በአጠቃላይ የገጠሩ ህብረተሰብ ከድህነት የሚላቀቅበትን መንገድ ለሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎች ከድህነት የሚላቀቅበትን መንገድ ለሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎች የሚውል ሲሆን በተለየ ሁኔታ ሴቶችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ተገልጧል፡፡

በአመዛኙም ለሴቶች ዘርፈ ብዙ የስራ እድሎችን ለመፍጠር ያገለግላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በአሁን ሰዓት በኢትዮጵያ የገጠር አካባቢ ነዋሪ ከሆኑ መካከል 15 በመቶ የሚሆኑት ብቻ የቁጠባ ባህል ያላቸው ሲሆን ቀሪዎቹ የእለት ጉርሳቸውን እንኳ ለማግኘት የታደሉ አለመሆናቸው በተዘገባው ተመልክቷል፡፡